

እጮኝነትና ጋብቻ

በልዑልሰገድ ለማ (2010 ዓ.ም)

ማውጫ

ገጽ

መግቢያ.....

ምዕራፍ 1 ጓደኝነትን መረዳት.....

የጓደኝነት ትርጉም

የጓደኝነት አይነቶች

ጓደኝነትና ተጽዕኖ

የተቃራኒ ጾታ ጓደኛ ፍለጋ መርሆዎች

ምዕራፍ 2 እርጫኝነት.....

እጮኝነት ምን ማለት ነው?

የፍቅር ጓደኝነት መቼና ማንን?

የፍቅር ጓደኝነት ጊዜ

እጮኝነትና መስፈርት

እጮኝነትና የጌታ ፈቃድ

እጮኝነትና ትዳር

የፍቅር አይነቶች

የእጮኝነት በረከቶች

የእጮኝነት ተግዳሮቶች

ምዕራፍ 3 ጋብቻ.....

የጋብቻ ትርጉም

የጋብቻ ዓላማ

የጋብቻ ዓላማ ያልሆኑ ነገሮች

የባልና የሚስት ኃላፊነቶች

ተግባቦት በትዳር ውስጥ

የጋብቻ ህይወት እውነታዎች

የጋብቻ ህይወት መርሆዎች

የጋብቻ ህይወት በረከቶች

የጋብቻ ህይወት ተግዳሮቶች

ምዕራፍ 4 የቤተሰብ ህይወት.....

የአባትና የእናት ኃላፊነቶች

ልጆችን የማሳደግ ጥበብ

ለልጆች አታድርጉ!

ዋቢ መጽሐፍት.....

መግቢያ

እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረ በኋላ ሰውን በመልኩና በአምሳሉ ፈጠረ። ይህ የተፈጠረው ሰው ዕድሜው ምን ያህል ይሆን? ህጻን ወይስ ወጣት፣ ገምቱ። ሽማግሌ ይመስላችኋል? የተፈጠረው ሰው ዓለምን እንዲያስተዳድር ለጋብቻም ብቁ ሆኖ ነበር። ስለዚህ አዳም ሲፈጠር ወጣት ነበር ማለት ነው። በወጣትነት ብዙ ነገር ይጠብቀናል። እኛ ወጣቶች ለሁሉም ነገር ዝግጅት ማድረግ አለብን። ጸሐፊው ይህንን ታሳቢ በማድረግ ለአሁኑ ወጣቶች ለነገው ቤተሰብና ሀገር ተረካቢዎች ይሆን ዘንድ እችን ትንሽ መጽሐፍ አበርክቷል።

ወጣትነት ማንም ወንድም ሆነ ሴት ማምለጥ የማይችልበት የፈተና፣ የመሳሳብና የመፈላለግ ጊዜ ነው። ከተቃራኒ ጾታ ጋር ለመሄድ ይወዳሉ። በወጣቶች ልብ ከሚመላለሱት ጥያቄዎች አንዱና ዋነኛው የወደፊት የትዳር ጓደኛ ጉዳይ ነው። ማንን ይሆን የማገባው? ምን አይነት ትዳር ያጋጥመኝ ይሆን? መቼ ይሆን የማገባው? የሚሉ ወሳኝና አንገብጋቢ ጥያቄዎች በውስጣቸው ዘወትር ይንከባለላሉ።

የዚህ ትንሽ መጽሐፍ ይዘት በአራት ዋነኛ ነገሮች ማጠቃለል ይቻላል። ጓደኝነት፣ እጮኝነት፣ ጋብቻና የቤተሰብ ሕይወት እነዚህን በማንሳትና በማብላላት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከቶችን ያንጸባርቃል። እንዲሁም አነጋጋሪ ጉዳዮችን ለማንሳት ይሞክራል።

ከወንድም ልዑልሰገድ ለማ

ለአስተያየት ወይም ለጥያቄ በተገለጸው አድራሻ ያድርሱን፡-

E-mail፡ leullema2008@gmail.com

Facebook፡ Leulseged Lema

Phone: +251-919-7417-00

ማሳሰቢያ!

አብዛኞቹ በወንድ ጾታ የተገለጹት ለሴት ጾታም እንደሚሆኑ አሳውቃለሁ። እንዲሁም ሰው ቢየ የገለጽኩት ሁለቱንም ጾታ የሚወክል መሆኑን እንድታውቁ እወዳለው።

መልካም ንባብ!

ምዕራፍ 1 ጓደኝነትን መረዳት

የጓደኝነት ትርጉም

ጓደኝነት ማለት እጮኝነት ማለት አይደለም፡፡ ለአንድ ሰው አምስት ጓደኞች ቢኖሩ አምስት እጮኞች አሉት ማለት አንችልም፡፡ ጓደኝነት የክፍል፣ የቤተክርስቲያን፣ የሰፈር....ወዘተ ትውውቅን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ጓደኝነት የተመሳሳይም የተቃራኒ ጾታ ትውውቅና ህብረት ሊሆን ይችላል፡፡ እጮነት ግን ከጓደኝነት ከፍ ያለ ነው፡፡ ስለዚህ ጓደኝነትማለት በተወሰኑ ነገሮች የተፈጠረ ህብረት ነው፡፡

Sis/Bro → Relation Ship → Engagement → Marriage → Family Life

የጓደኝነት አይነቶች

1. **የስራ ጓደኛ**- በስራ መስክ ላይ የተመሰረተ ጓደኝነት ነው፡፡
2. **የትምህርት ጓደኛ**- በትምህርት ቤት የተመሰረተ ጓደኝነት ነው፡፡
3. **የእምነት ጓደኛ**- በቤተክርስቲያን የሚተዋወቁ ሰዎች የመሰረቱት ጓደኝነት ነው፡፡
4. **የሰፈር ጓደኛ**- በሰፈር የሚተዋወቁ እና ህብረት የሚያደርጉ ጓደኝነት ነው፡፡
5. **የተቃራኒ ጾታ ጓደኛ/የፍቅር ጓደኛ**- ከሌሎች ጓደኝነት ለየት የሚያደርገው ወደ እጮኝነት ሊያድግ ስለሚችል ነው፡፡ በተለምዶ Relationship ተብሎ ይታወቃል፡፡

ጓደኝነትና ተጽዕኖ

"ብረት ብረትን ይስለዋል ሰውም ባልንጀራውን ይስላል" ይላል ቅዱስ ቃሉ(ምሳ 27:17)፡፡ መቼም ቢሆን ሰው ከጓደኛው ጋር ሲገናኝ በመልካምም ሆነ በክፉ ተጽዕኖ ይደረጋል፡፡

አንድ የሳይኮሎጂ ምሁር በአንድ ወቅት "ስለ ጓደኛህ ንገረኝ እኔም ስለአንተ እነግርሃለው" ብሎ ነበር፡፡ በጣም ትክክል ነው፡፡ ይህ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ የሐዋሪያትን ህይወት መመልከት በቂ ነው፡፡ ያልተማሩት ጴጥሮስና ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር ስለዋሉ በኢየሱስ ተስለው ነበር፡፡

"ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ ጊዜ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደነቁ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ አወቁአቸው።"(ሐዋ 4:13)

እውቀትን መሰረት አድርገን ስናይ ሦስት አይነት ሰዎች አሉ

1ኛ ከእኛ የሚበልጡ፣

2ኛ ከእኛ ጋር በእኩል ደረጃ ያሉ፣

3ኛ ከእኛ የሚያንሱ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በእምነት ወይም በእውቀት የደከሙትን አግዙአቸው/እርዷቸው ይለናል፡፡ ይህ ማለት ከማያምነት ጋር ማለት አይደለም፡፡ ከእኛ የሚያንሱ ስል በቃሉ መረዳት ወይም በመንፈሳዊነት ሊሆን ይችላል፡፡

ከፍታማ ቦታ ላይ ያለን ሰው ዝቅታማ ቦታ ላይ የሆነ ስቦ ሊያወርደው ይችላል፡፡ ምክንያቱም ወደታች ለመሳብ ቀላል ስለሆነ፡፡ ስለዚህ ከእኛ በእምነት ወደሚያንሱትጋ ስንሄድ መጠንቀቅ አለብን፡፡ ጠንካሮች ሆነን ነው ሌሎችን መርዳት ያለብን፡፡ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ ስለምል ቃሉ፡፡" (1ኛ ቆሮ 10፡12)

ከእኛ ጋር እኩል ወደሆኑትጋ ስንሄድ ደግሞ መረዳታቸውን መካፈል፣ ያለንን የህይወት ልምምድ፣ የቃል መረዳት እንዲሁም መልካም የሆነ ነገር በሙሉ ማካፈል አለብን፡፡ ስናካፍል ከእኛ እንዲበልጡ በማሰብ ይሁን፡፡ ይህ ነው በክርስቶስ ያለ ሀሳብ፡፡ ከእኔ የሚበልጥ ትሰራላችሁ እያለ ሐዋሪያትን ሲያስተምራቸው ነበር፡፡ ሐዋሪያት የበለጠ እንዲሰሩ መንፈሱን በማደል አረጋግጧል፡፡

ከእኛ ወደሚበልጡትጋ ስንሄድ መስማትና በህይወታቸው ካሳለፉት ስኬታቸውና ውድቀታቸው መማር አለብን፡፡ ይህ ለእኛ ለቀጣዩ ጉዞአችን እንደ መኪና "ስፖኪዮ" ያገለግለናል፡፡

የተቃራኒ ጾታ ጓደኛ ፍለጋ መርሆዎች

1. **በጸሎት እግዚአብሔርን መጠየቅ-** እፎኝነት ከመጀመራችን በፊት ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ እርሱም ጸሎት ነው፡፡ የውስጥ ውበት የሚታየው በጸሎት ነው(ምሳ 31፡30)፡፡ **"መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ....እርሱም ያደርግልሃል፡፡"** የአብርሃም ሎሌ ለጌታው ልጅ ለይስሃቅ ሚስት ሊመርጥለት በእግዚአብሔር ታምኖ ተንቀሳቀሰ(ዘፍ 24፡27)፡፡ እግዚአብሔርን "ምራን?" ካልነው ይመራናል፡፡ ጸሎት እፎኝነት ለመጀመር ብቻ ሳይሆን በህይወት ዘመን ሁሉ የሚያስፈልግ ነገር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

   ወደ ጎን ዞር ዞር ከማለታችን በፊት ወደ ሰማይ ማየት መልካም ነው፡፡ ለምን? ስባል እግዚአብሔር ልባም ሴት እንድናገኝ ይረዳን ዘንድ፡፡ ቃሉ እግዚአብሔር ልባም ሴት ያገኝላችኋል አይልም፡፡ ወይም ልብም ሴት ይጠይቅላችኋል አይልም፡፡ እኛ ነን ልባም ሚስት የሚናነነው፣ እኛ ነን "የምንጠብሰው"፡፡ በአንድ ዓይናችን ጨፍነን በአንድ አይናችን ገልጠን ማየት አለብን፡፡

2. **መስፈርት ማስቀመጥ-** **"...ለጻድቃንም ምኞታቸው ትሰጣቸዋለች፡፡" (ምሳ 10፡24)** አንድ አይነት ላባ ያላቸው በአንድ ላይ ይበራሉ፡፡

3. **ታላቅ እንቅልፍ ማንቀላፋት-** ታላቅ እንቅልፍ የሚያሳየው የሚያዘጋጀው እግዚአብሔር መሆኑን እያረጋገጥን እንደሆነ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ጭንቀት የለሌበትና ፊጹም እረፍት ምልክት ነው፡፡ ከተሰጠን ራዕይ ጋር የምትሆነን ሚስት የምናሰላሰልበት ምዕራፍ ነው፡፡ **"...በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ፡፡" (ፊል 4፡6)**

4. **ዓይን መግለጥ-** ዓይን መግለጥ ሁለት አውዶችን ያካተተ ነው፡፡ የመንፈስ ዓይንና የስጋ ዓይንን መግለጽ ያካትታል፡፡ መጀመሪያ የውስጥ ዓይናችንን መግለጥ አለብን፡፡

5. **ማጣራት-** የትዳር አጋርን መፈለግ ኃጥአት አይደለም፡፡ ወንዶች ከሆንን በዙሪያችን ካሉ እህቶች ለተቃራኒ ጾታ ንጹህነት የሚሆኑትን በሁለቱ ዓይኖቻችን አይተን መምረጥ፡፡

ምዕራፍ 2 እጮኝነት/Engagement

እጮኝነት ምን ማለት ነው?

የተቃራኒ ጾታ ጓደኝነት ዘመን-አመጣሽ ወይም ሰይጣን እኛን ለማጥመድ ያመጣው ነገር ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ውስጥ የነበረ ነው። እጮኝነት ወደ ትዳር መግቢያ በር ነው። እጮኝነት ማለት አንድ ሰው ራሱን ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው ለመስጠት የሚዘጋጅበት የህይወት ምዕራፍ ነው። ይህ ያለፈውን፣ የአሁኑንና የወደፍቱን ህይወት መጠናናትን ያጠቃልላል። እጮኝነት ሁለት ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ሰዎች ለመጋባት ወስነው የሚቆዩበት ጊዜ ነው። እንዲሁም ደግሞ እጮኛኝነት የሚጋቡበትን ጊዜ የምወስኑበት ምዕራፍና ለትዳር ህይወታቸው መሰረት የሚጥሉበት ጊዜ ነው። ስለዚህ እጮኝነት ከተቃራኒ ጾታ ጓደኝነት/Relationship ከፍ ያለ ነው።

የፈቅር ጓደኝነት መቼና ማንን?

<u>የፍቅር ጓደኝነት መቼ?</u>

የፍቅር ጓደኝነትን ለመጀመር ትክክለኛ ጊዜውን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። የብዙ ሰዎች ጓደኝነት ትዳር ላይ ሳይደርስ ከሚፈርስባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ያለጊዜው መጀመሩ ነው። ጓደኝነትን ያለጊዜ በመጀመር ከሚደርሱት ጉዳቶች ውስጥ ደግሞ ዋነኛው የቅድስና ችግር ነው። "አንድ ሰው የፍቅር ጓደኝነትን መቼ መጀመር አለበት?" የሚለው ጥያቄ በስነ መለኮት ምሁራን ዘንድ ተመሳሳይ መልስ ባያስገኝም፣ ብዙዎች የሚስማሙት በሦስት መሰረታዊ ቅድሜ ሁኔታዎችን ነው፡-

1ኛ መንፈሳዊ ብስለት- Spiritual Maturity

መንፈሳዊ ብስለት ለማንኛውም ዳግም ለተወለደ ክርስቲያን ሁሉ አስፈላጊ እና ወሳኝ ነገር ነው። የፍቅር ጓደኝነትን ለመጀመር ደግሞ በይበልጥ መንፈሳዊ ህይወታችን ያደግን እና የበሰልን ልንሆን ያስፈልጋል። ምክንያቱም ህይወት መንፈሳዊ በመሆኑ።

ስለዚህ መንፈሳዊ የሆነውን ህይወት ለመምራት በመንፈሳዊነት መጠንከር አለብን። በመንፈሳዊ ህይወት የጠነከረ ሰው የፍቅር ጓደኝነት ብጀምር ጥሩ ነው።

አንድን ሰው በመንፈሳዊ ነገር ጠንክሯል የምንለው አዘውትሮ ወደ ቤተክርስቲያን ስለሄደ አይደለም። መንፈሳዊነት የሚለካው መንፈሳዊ ህይወቱን የሚፈትኑ ፈተናዎች ስመጡ በቃሉና በመንፈሱ ማለፍ ስችል ነው።

2ኛ የአዕምሮ ብስለት- Mental Maturity

የፍቅር ጓደኝነትን ለመጀመር የአዕምሮ ብስለት በጣም አስፈላጊ ነው። አንድ ሰው ጓደኝነቱን እንዴት በቅድስና መጠበቅ እንዳለበት፣ ያለ ምንም እንቅፋት እንዴት ወደ ትዳር ማድረስ እንዳለበት፣ ሰዎችን ላለማሰናከል ምን ማድረግ እንዳለበት....ወዘተ ለማወቅ የአዕምሮ ብስለቱና ዝግጁነቱ አናሳ ከሆነ ስኬታማ የፍቅር ህይወት አያጣጥምም። ከዚህም ባሻገር በትዳር ህይወት ስለ

ቤት አስተዳደር፣ ስለ ገንዘብ አያያዝ፣ ስለ ልጆች አስተዳደግ፣ ስለ ስራ ፈጠራ....ወዘተ ለማወቅ የአዕምሮ ብስለት ወሳኝ ነገር ነው።።

3ኛ የአካል ዕድገት- Physical Maturity

የአካል ዕድገት ማለት ለአቅመ አዳም/ሔዋን የመድረስ ጉዳይ ነው።። ምንም እንኳን ሴቶች እዚህ ደረጃ ላይ ቀድመው ደርሰው ቢገኙም ነገር ግን በአማካኝ ለወንድም ለሴትም ከ18 ዓመት በላይ ሲሆኑ ነው።።

በዓለም ዙሪያ ታዋቂ አገልጋዮች የሚስማሙት እነዚህን ሦስቱን ያሟላ ሰው የፍቅር ጓደኝነት ሊጀምር ይችላል ይላሉ።። ለመጋባት ደግሞ ተጨማሪ 4ኛ መሰረታዊ ፍላጎታቸውን/Basic Needs የሚያሟሉ ሊሆኑ ይገባል።። እነዚህም ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ናቸው።።

<u>ለፍቅር ጓደኝነት ማንን?</u>

በውጫዊ ነገር ላይ ተመርኩዞ የሚደረግ ውሳኔ ስህተት ላይ ይጥላል(1ሳሙ. 16፡7)።። ውጫዊ መመዘኛ ተጠቅመን ትክክለኛ ትዳር ልንመሰርት አንችልም።። ምክንያቱም ጋብቻ የውጫዊ አካል መጣጣም ሳይሆን የውስጥ መጣጣም ስለሆነ ነው።። ስለዚህ በምርጫ ወቅት በእግዚአብሔር ላይ መታመን አለብን።። አስተዋይ ሴት ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት(ምሳ 19፡14) ገንዘብን ማዕከል ያደረገ የፍቅር ጓደኝነት በትዳር ወቅት ገንዘቡ ሲጠፋ ከትዳር ዘሎ መውጣትን ያስበል።። ጸንቶ የሚኖረው ገንዘብ ሳይሆን ፍቅር ብቻ ነው።።

የፍቅር ጓደኝነት ወደ እጮኝነት መግቢያ በር ነው።። እጮኝነት ደግሞ የጋብቻ በር ነው።። ሁለት ተቃራኒ ጾታዎች ወደፊት እንጋባለን ብለው ስለማመ ህብረታቸው ከፍቅር ጓደኝነት/Relationship ወደ እጮኝነት/Engagement ይሸጋገራል።። በዚህን ወቅት የፍቅር ጓደኝነታቸው በእጮኝነት ይጠቃለላል።። እጮኝነት ከውስጥም ከውጭም መክፈቻ ያለው በር ይመሳሰላል።። ትዳር ደግሞ ከውጪ ብቻ መክፈቻ ያለው፤ ከገቡ በኋላ በውስጥ መክፈቻ የሌለው በር ይመስላል።። ከጋብቻ በኋላ ለማምለጥ መስኮትንም መፈለግ ሞኝነት ነው።። እጮኝነት ህብረት ሊቋረጥ ይችላል፤ የጋብቻ ፍቺ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው።። ስለዚህ የፍቅር ጓደኝነት ለእጮኝነትና ለጋብቻ ህይወት መሰረት በመሆኑ በዚህ የህይወት ምዕራፍ ላይ ቆም ብለን ራሳችንን መመልከት ብልህነት ነው።።

መጽሐፍ ቅዱስን "ማንን ላግባ?" ብለን ብንጠይቀው "ክርስቲያን አግባ/ቢ" ይላል።። ይህ የተገለጠ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።። አንዳንዶች ጓደኛየ "ጴንጤ እሆናለሁ" ብላለች እያሉ ወንጌል አሰራጫለው በሚል ሰበብ ተሰራጭተው የቀሩ ጥቂት አይደሉም።።

የፍቅር ጓደኝነት ጊዜ

የፍቅር ጓደኝነት ጊዜ ምን ያህል መሆን እንዳለበት ግልጽ የሆነ መመሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማግኘት ባይቻልም እንኳን እግዚአብሔር በሰጠን ጤናማ አዕምሮ በመጠቀም ተመጣጣኝ ጊዜ መቆየትና በአግባቡ መጋባት ተገቢ ይሆናል።። በእጮኝነት ወቅት እንደ ባልና ሚስት በመሆን የፊለጉትን ስጋዊ ፍላጎታቸውን የሚፈጽሙ አይጠፉም።። እንደዚህ አይነት አቋም በእግዚአብሔር ፊት አጉል ድፍረት ከመሆኑም በላይ ተጋቢዎችን ህሊና ክፉኛ የሚያቆሽሽ ለሌሎችም መሰናክል የሚሆን እርምጃ ነው።። ምክንያቱም መተጫጨት ማለት መጋባት ማለት አይደለም።።

በእጮኝነት ሰዎች ብዙ ዓመታትን ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ በዚህ በእጮኝነት ጊዜ የሚያሳልፉት የቅድስና ህይወት የወደፊት ትዳራቸውን ምን እንደሚመስል ይተነብያል፡፡ ስለዚህ የእጮኝነትን ጊዜ በጥንቃቄና በጽዱ ኃጄኝነት እንዲሁም ነውርና ነቀፋታ በሌለው አካሄድ በመያዝ ህደት ውስጥ የሚከተሉት ጥያቄዎች መጠየቅ አስተዋይነት ነው፡፡

1. በመካከላችን እውነተኛ ፍቅር አለ ወይ?
2. የዓላማ አንድነት አለን ወይ?
3. ባህሪዋን/ውን አውቃለው ወይ?

እጮኝነትና መስፈርት

መስፈርታችን ውስን ሊሆኑ ይገባል፡፡ ብያንስ እኛ የሚናሚላቸውን ነው ከተቃራኒ ጾታ መጠበቅ ያለብን፡፡ የዕድሜ ልዩነት ጉዳይ በተመለከተ በጣም እንዳያንስና እንዳይበዛ መጠንቀቅ መልካም ነው፡፡ የተቀራረበ ዕድሜና የትምህርት ደረጃ ቢሆን ይመረጣል፡፡

የአንዳንዶች መስፈርት A-Active B-Beautiful C-Clever D-Disent E-Exellent F-Fantastic .....በማለት እነዚህን በሙሉ የሚታሚላ እጮኛ እፈልጋለው እያሉ ዘግይተው "ወንድም ዘገየ" የሚል ቅጥያ ስም የተሰጣቸው ጥቂት አይደሉም፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርቶች እነሆ፡-

1. **ክርስቲያን-** የተቃራኒ ጾታ ኃጄኝነት ከመጀመራችን በፊት በአንድ መንግስት መሆኑን/ኗን ማረጋገጥ አለብን(አሞ 3፡3)፡፡ ዳግም የተወለደ/ች ክርስቲያን የመጀመሪያ መስፈርታችን እናድርግ፡፡ ያለበለዚያ ያለውን ልዩነት ተመልከቱ፡-

ኢየሱስ (ቆላ 1፡13)	ሰይጣን (2ኛ ቆሮ 6፡14-16)
አማኝ	የማያምን
ጻዲቅ	ኃጢአተኛ
ብርሃን	ጨለማ
ታቦት	ጣአት
ክርስቶስ	በልሆር

ወደፊት የምታገቡት ዳግመኛ የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ካልሆነ የማን ልጅ እንደሚሆን መንገር አያስፈልግም፡፡ ስለዚህ አባቷ ወይም አባቱ ሰይጣን ልጁን ለመግብኘት ወደዚህ ቤት በየጊዜው ብቅ ማለቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ሰይጣን አዘውትሮ በምጎበኘው ቤት መኖር ትፈልጋላቸው?

2. **የውስጥ ውበት-** ውስጣዊ ውበት የሚጀምረው እግዚአብሔርን በመፍራት ነው፡፡ እግዚአብሔርን የሚታከብር ሚስት ለባሏ ትገዛለች፡፡ የውስጥ ውበት ርህራሄ፣ እምነት፣

መንፈሳዊ ዕውቀት ሲሆን። ይህ ደግሞ በሴቶች መካከል ብንመለከት ታላቅ "ሴት ያሰኛታል"(2ኛ ነገ 2፡8)።

3. **የውጪ ውበት-** በትዳር ጓደኛ ምርጫ ወቅት ውበት የማይርቅ ድርሻ ያለው ቢሆንም እንኳ በውስጣዊና በውጫዊ ውበት መካከል ሚዛን መጠበቅ አለብን። በተለይም ደግሞ ለውስጣዊ ውበት ትኩረት መስጠት አስተዋይነት ነው(ምሳ 31፡30)። ውጫዊ ውበት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከሰመ የሚሄድ ሲሆን ውስጣዊ ውበት ግን በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ነው።

የፍቅር ጓደኛ ስንመርጥ በደንብ መጠንቀቅ ያለብን፡-

1. **ህልም-** በህልም ተመስርቶ የፍቅር ጓደኛ መምረጥ አደገኛ ነው። መጽሐፍ በመክበብ አምስት ቁጥር ሶስት ላይ ህልም በስራ ብዛት ይታያልና ይላል። አንድ ሰው ቀኑን ሙሉ ስለ ተቃራኒ ጾታ ቢያሰላስል በህልም የማየቱ ዕድል ሰፊ ነው። ለምሳሌ አንድ ክርስቲያን ወንድ በህልም ከማታምን ሴት ጋር ሲጋባ ቢያይ የጌታ ፈቃድ ነው ማለት አንችልም። ስለዚህ በፍቅር ጓደኛ ምርጫ ወቅት ህልምን መጠንቀቅ አለብን። ምክንያቱም ከማያምኑ ጋር አትጠመዱ የተባለው የጸና ቃል በህልም አይሻርም።

   አንዳንድ ወንዶች እግዚአብሔር እንዲጠይቅሽ አስጨንቆኝ ነው፣ እምቢ ብትይ አንችንም ያስጨንቅሻል፣ በህልሜ አበባ ስትሰጭኝ፣ ወንዝ ስንሻገር፣ በአንድ ጽዋ ስንጠጣ አየሁ። እያሉ እህቶቻችንን ግራ የሚያጋቡት ምን ነክቷቸው ነው እላለሁ? አንዳንዶች ግራ ተጋብተው ሲሆን ሌሎች ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ስም የሚዘረጉት መረብ ነው። ሴቶች የወደዱትን ወንድ የማግባት ህገ-መንግስታዊም መጽሐፍ ቅዱሳዊም መብታቸው ነው።

   የዘላለም ህይወት ለመስተት ማስጨነቅ ብችልም በፍቅር ሳያስጨንቀን የሰጠን ትሁቱ አባታችን እንዴት በትዳር ጉዳይ ፈቃዳችንን ይጋፋል? በፊጹም በህልም አያስገድደንም።

2. **ትንቢት-** ትዳር በትንቢት አይመሰረትም፣ ደግሞም አይፈርስም። እግዚአብሔር በትንቢት አቅጣጫ ሊያሳየን ይችላል ነገር ግን እግዚአብሔር በትንቢት "ካላገሃት ወይም ካላገባሽ እንዲህ አደርጋለው" ብሎ በፊጹም አያስፈራራም።

3. **እሺ አለማለት-** ወንዶች አፈቀሩኝ ብለው ሴቶች የሚመጻደቅት ነገር አላቸው። "እፍፍ" በማለት የፍቅርን እሳት አንድደው ለወንዶች ብርቱ ተስፋ ከሰጡ በኋላ ድንገት ቀኝ ኋላ የሚዞሩ እንዳሉ እኛ ወንዶች እናውቃለን። አንዴ አንዲህ ሆነ አንዲት ቆንጆ አንዱን ሸበላ ዳር ዳር ስትል ቆየችና አፍ አውጥታ "እወድሃለው" አለችው። እርሱም ወዲት ስለነበር የፍቅርን ቀጠማ አብረው መቀንጠስ ጀመሩ። ብዙ ጊዜ አልቆዩም ድንገት አንድ ቀን ከመሬት ተነስታ "እወድሃለው ያልኩህ ውሸተን ነው" አለቸው። ልጁ ሰማይ ምድሩ ተደበላለቀበት። ቢሆንም ውሳኔውን ከመቀበል ምርጫ አልነበረውም። ሌላ ጊዜ ድንገት መጣችና "ውሸቴን ነው ያልኩህ ውሸቴን ነው" አለችው። ይህንስ ምን ይበል? የቱን ይመን? አሁንስ ቢሆን "*ውሸቴን ነው ያልኩህ ውሸቴን ነው ያለቸው ውሸቷን እንዳልሆነ*" በምን ማረጋገጥ ይችላል? ለመሆኑ ፍቅር እውነት ካልሆነ ምን እውነት ሊሆን ነው? ፍቅር አውነት ካልሆነ ህይወትም እውነት አይሆንም በፍቅር ቀልድ የለም።

   ለፍቅር የማይንበረከክ ሰው የለም! የኢየሱስ አገልጋይ የሆንነው ፍቅሩ ስላስገደደን ነው። ለፍቅር ጓደኝነት ስንጠይቅ እሺ ላይሉን ይችላሉ። መፍትሄው መስተፋቅር ሳይሆን ማፍቀር

ነው፣ አሁንም ማፍቀር፣ አሁንም ማፍቀር፣ አሁንም ማፍቀር። ብቻ በጥበብና በማራኪነት ይሁን! ፍቅርን በጥበብ ማካፈል ከመስተፋቅር ይበልጣል። ጸሐፊው በሚማርበት ዲላ ዩንቨርስቲ አንዳንድ ወጣት ዓለማውያን መስተፋቅር እንደሚጠቀሙ ተደርሷል። መስተፋቅር የሚጠቀሙ በሰይጣን ትዕዛዝና ራስ ወዳዶች እንደሆኑ ግልጽ ነው። በአማኞች ላይ መስተፋቅር አይሰራም። የተጠቃሚዎችም መጨረሻ ጥፋት ነው።

4. **አለመተዋወቅ-** ብዙ ጊዜ ወንዶች የሴቶችን ፊት ፈገግ ብሎ ካዩ ያፈቀሯቸው ይመስላቸዋል። ወዲያው ፍቅራቸውን ያካፍላሉ። በተቃራኒው ደግሞ አንዳንድ ወንዶች ደግሞ ያፈቀሩትን የማይለዩ፣ ቦምብ ቢፈነዳ የምልክት ቋንቋ የማይገባቸው አሉ።

   ወንዶች ራሳቸውን መጠየቅ ያለባቸው "ስለ እኔ በደንብ ታውቃለች ወይ" ብለው ነው። በደንብ ከተተዋወቁ ለእጮኝነት ሲጠየቁ ለመልስ ይቀላቸዋል። ስለዚህ ከፍቅር ጥያቄ በፊት ብያንስ የተወሰነ መተዋወቅ አለባቸው።

እጮኝነትና የጌታ ፈቃድ

ብዙ አማኞች እጮኝነትን በተመለከተ የጌታን ፈቃድ ለማወቅ ይጠይቃሉ። ተገቢና የጌታን ምሪት የመፈለግ ጥያቄ ነው። ደግሞም በዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማወቅ በጣም ይጠቅማል። ሀሳቡም በጎና ያማረ በመሆኑ(ኤር 29፡11)።

የጌታ ፈቃድ መሆኑን የምናውቅበት ሁለት መንገዶች፡-

1. **በቃሉ-** የእግዚአብሔር ፈቃድ በቃሉ ግልጥ ሆኖ ተጽፏል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ሁሉም መልስ አወን ይሆናል።

1. ክርስትያን ነው/ናት	አወን
2. ተቃራኒ ጾታ ናቸው	አወን
3. ትዋደዳላችሁ	አወን
4. የደም ዝምድና የላችሁም	አወን
100%	100%

2. **በውስጥ ምስክርነት-** የውስጥ ምስክርነት የመንፈስ ቅዱስ ድምጽ ምስክርነት ነው።

እጮኝነትና ትዳር

እጮኝነት ራሱን የቻለ ህይወት ነው፣ ትዳርም እንዲሁ። እጮኝነት የነፍስ(እውቀት፣ ስሜት፣ ፈቃድ) ትውውቅና አንድነት የሚፈጠርበት ህይወት ሲሆን ጋብቻ ደግሞ የመንፈስ፣ የነፍስና የስጋ አንድነት የሚፈጸምበት ህይወት ነው። እጮኝነት ሊቋረጥ ይችላል። የእጮኝነት በር የተቃራኒ ጾታ ፍቅር ሲሆን፣ የጋብቻ በር ደግሞ እጮኝነት ነው።

የእርጭኝነት ጊዜ ዓላማው መጠናናት ነው፡፡ በእርጭኝነት ጊዜ ወንድ ሴቷን ሚስቴ ማለት አይችልም፡፡ ከፈለገ የወደፍቴ ሚስቴ ሊላት ይችላል፡፡ ምክንያቱም ተጫጨ ማለት ተጋቡ ማለት አይደለም፡፡

የእርጭኝነት ህይወት የራሱ የሆኑ የፍቅር መግለጫ መንገዶች አሉት፡፡ ለምሳሌ፡-

- ስጦታ በመሰጣጣት፣
- አብሮ ጊዜ ማሳለፍ፣
- በመዝናናት፣
- ፍቅርን በመግለጽ(በድምጽ፣ በሚሴጅ).....ወዘተ

የትዳር ህይወት የእርጭኝነትን የፍቅር መግለጫ ያካተተና ተጨማሪ ሌሎች ያሉት ነው፡፡ ለምሳሌ፡-

- ልጆችኝ በማንከባከብ፣
- በሰውነት ንክክ፣
- በወሲብ.....ወዘተ

የፍቅር አይነቶች

- **አጋፔ/Agape-** ከሁሉም ፍቅር አይነቶች ከፍና ላቅ ያለ ነው፡፡ በነገሮችና በሁኔተዎች ላይ ያልተመሰረተ፣ እውነተኛ ፍቅር ነው፡፡ ቸር የሆነ ከሰዎች ምንም የማይጠብቅ ነው(0% Expectation) የዚህ ፍቅር መሰረቱ እግዚአብሔር ነው፡፡ በሌላ አጠራሩ የእግዚአብሔር ፍቅር ተብሎ ይጠራል፡፡

  በበደላችንንና በኃጢአታችን ሙታን በሆነን ጊዜ እግዚአብሔር እኛን በማፍቀሩ ይህንን የአጋፔ ፍቅሩን ገለጠልን፡፡ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነን እያለን ከእኛ ምንም ሳይፈልግ በራሱ አደረገ፡፡

- **ኢሮስ/Eros-** በተቃራኒ ጾታ መካከል ያለ ፍቅር ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ በረከት ነው፡፡ የዚህ ፍቅር መሰረት አጋፔ ፍቅር መሆን አለበት፡፡

- **ስቶርጂ/Storge-** የደም ዝምድና ባላቸው ቤተሰብ መካከል ያለ ፍቅር ነው፡፡ መሰረቱ የሆርሞን/Hormone አንድነት ነው፡፡

- **ፒሊዮ/Phileo-** በአማርኛ "እንካ በእንካ" ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ ፍቅር የተመሰረተው በመስጠትና በመቀበል መርህ ላይ ነው፡፡ በአማኞች መካከል ይህ ዓይነት ፍቅር እንዲኖር አይፈለግም፡፡

የእጮኝነት በረከቶች

- **መጠናናት-** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያዕቆብ ራሄልን ይወዳት ነበረ፡፡ እርሷን ለማግባት 7 ዓመት ለአባቷ ላባ አገልግሎት ሰጥቶ ነበር፡፡ በሠርግ ቀን ማታ ላባ በአገሩ ባህል መሰረት ፊቷን በጨርቅ ሸፍነው ያልወደዳትን ያልመረጣትንና ከእርሱ ጋር ብዙም ንግግር የሌላትን የራሄልን እህት ልያን አስረከቡት፡፡ ያዕቆብም በማግስቱ ተነስቶ ቢያያት ያገባት ሚስት የሚወዳት ራሄል ሳትሆን ቀርታ ልያ ሆና አገኛት(ዘፍ 29፡16-25) አንብቡ፡፡ በሁኔታው ያዕቆብ ምን ያህል ተቆጥቶ ይሆን? በአሁን ዘመንም የምናገባቸው የትዳር ጓደኞቻችን በፊት በእጮኝነት ጊዜ ራሄልን መስለው በሰርጉ ማግስት ሁኔታቸው ሁሉ ተቀይሮ እንደ ልያ የማንወደውን ስናይ እንደነቃለን፡፡ ስለዚህ ባገባችሁ የትዳር ጓደኛ ከሰርግ በፊት ያልነበረ ጸባይ ሊመጣ ስለሚችል ከጋብቻ በፊት በደንብ መጠናናት ጥቅሙ ብዙ ነው፡፡

  በአሜሪካን ሀገር በተደረገ ጥናት መሰረት "ከተጋቢዎች 80% በላይ በደንብ የሚተዋወቁት ከተጋቡ ከሦስት ወር በኋላ ነው" ይላል፡፡ "ብልጥ ሰው ከሌላ ሰው ስህተት ይማራል ሞኝ ሰው ደግሞ ከራሱ ስህተት ይማራል" ይላሉ የሀገሬ ሰዎች፡፡ ስለዚህ የእጮኝነት ጊዜ ለመጠናናት ወሳኝ ምዕራፍ ነው፡፡

- **መወያየት-** በእጮኝነት ወቅት መወያየት ትልቅ ሚና አለው፡፡ አፍ ስከፈት ጭንቅላት ይታያል ይባላል፡፡ ሲወያዩ ጭንቅላታቸውን መተያየት ይጀምራሉ፡፡ በእጮኛሞች መካከል የአስተሳሰብ መመሳሰል የሚፈጠረው በመወያየት ነው፡፡ በዚህ ወቅት የሚነጋገሩት ስለ ፖለትካ፣ ስለ እምነት፣ ስለ ማህበራዊ ህይወት፣ ስለ ነገሮችና ስለ ራሳቸው ሊሆን ይችላል፡፡ መንፈሳዊያን የሆኑት በእጮኝነት ወቅት "ግላቲያ፣ ኤፌሶን፣ ቆሮንቶስ..." በማውራት ብቻ ጊዜው አሰልቺ እንዳያደርጉ ያስተውሉ፡፡ ለሁሉም ጊዜ አለውና፡፡ የውይይት ሀሳቡ ከሁለቱም ወገኖች ሆኖ በየዓይነት ቢቀርብ ይመረጣል፡፡

- **ጸሎት-** በእጮኝነት ወቅት አብሮ መጸለይ ወሳኝ ነው፡፡ ይህ ማለት ሰው የማይረብሽበት ዝግ ክፍል ፈልጎና እዛው በር ዘግቶ መጸለይ ማለት አይደለም፡፡ ፕሮግራም በለሌበት ሰዓት ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ስለ ህይወታቸውና ስለ አገልግሎታቸው በአንድነት መጸለይ በእጮኝነት ወቅት ወሳኝ ነው፡፡

- **ፍቅር-** እጮኝነት ራሱን የቻለ ህይወት ነው፡፡ ይህንን ህይወት ለማጣጣም ግብዝነት የለሌው ፍቅር ያስፈልጋል፡፡

የእጮኝነት ተግዳሮቶች

1. መዳራትና ዝሙት

በእጮኝነት ወቅት መሳሳም/Kissing ይፈቀዳል ወይ የሚል ጥያቄ ብዙዎች ይጠይቃሉ፡፡ መልሱ "በዲጥ ኳስ መጫወት ይቻላል ነው?" አንባቢም "ይከብዳል፤ ያዳልጣል" እንደምል እርግጠኛ ነኝ፡፡ መሳሳም የስሜት ህዋሳትን መቀስቀሻ ሞተር ነው፡፡ በዚህ ውስጥ የሰውነት መነካካት አለ፡፡ ይህ ደግሞ መዳራት ነው፡፡

የእጮኝነት ዓላማ ትዳር ስለሆነ ፈተናዎችን ማለፍ ይችላል፡፡ ነገር ግን በእጮኝነት ወቅት ፈተናው አይቀርም፡፡ ይህንን ፈተና ለማለፍ ከሁለቱም ወገኖች ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡ ጥንቃቄው ከሁለቱ ካልሆነ ማለፍ አይቻልም!!

በእጮኝነት ወቅት አጉል ጨዋታና ፈዝ ፍትወትን ስለሚቀሰቅስ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም አጉል ፊልም ወይም ስዕል ከፍተኛ ጥንቃቄን ይሻል፡፡ ከመጠን ያለፈ መላፋትና መተሻሸት ውድቀት ያስከትላል፡፡

Christian Research Institute ጥናት የሚነግረን እንደህ ነው፡- በዓለም ከጋብቻ በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈጽመው ከተጋቡት ውስጥ 90% ተፋተዋል ይላል፡፡ ምክንያቱን ሲያስቀምጥ፡-

1ኛ እውነተኛ ፍቅር ስላልሆነ ነው ይላል፡፡ እውነተኛ ፍቅር የራሱን አይፈልግም፤ ለመጥቀም እንጂ ለመጠቀም አያስብም፡፡ እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ስለሚፈልጉ ጥቅማቸውን ስያገኙ ይፋታሉ፡፡

2ኛ የሚፈልጉትን ቀድመው ስላገኙ ነው፡፡ የሚፈልጉት የውስጥ ውበት ስላልሆነ የውጪ ውበት ስረግፍ ፍቅራቸውም ይቀዘቅዛል፡፡

2. ራስን ሆኖ አለመገኘት

ይህ ችግር ብዙ ጊዜ በወንዶች ይታያል፡፡ ሁሉም ወንዶች የዚህ ችግር ተጠቂ ናቸው ለማለት ባያስደፍርም አብዛኞች ወንዶች በዚህ ይጠቃሉ፡፡ ሁለት "ጂንስ" ሱሪ ያለው ከፍቅር ጓደኛው ጋር ቀጠሮ ካለው የጓደኛውን ሱሪ ተበድሮ ይለብሳሉ፡፡ ጸሐፊው በሚማርበት ዲላ ዩኒቬርሲቲ የሚያስታውሰው አንድ ልጅ "ልዑሌ ብር አበድረኝ" ብሎ ተርበትብቶ የፊለገበትን ምክንያት እንኳ ለመናገር ጊዜ አጥቶ 200 ብር ተበድሮ እንደሄደ ያስታውሳል፡፡ ሲመለስ ለምንድነበር የተበደርከው ብሎ ሲጠይቀው መልሱ ምን ቢሆን ጥሩ ነው? "የፍቅር ጓደኛየ ጠርታኝ ነው" ብሎ እርፍ፡፡

በሰለን እንኳ ለመተኛት ወረፋ ይዘው የሚያድሩ ከቤተመንግት እንደሚወጣ በብድር ከመጠን በላይ ይዘንጣሉ፡፡ በሰለን ማደር ወይም መዘነጥ መጥፎ ነገር እንዳልሆነ ይሰመርበት፡፡ ያልተፈለገው ከመጠን በላይ በሆነ ጉራ የራስ ማስመሰሉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ራስን ማታለልና ራስን አለመቀበል ነው፡፡

ግልጸኝነት በእጮኝነት ወቅት ወሳኝ ነው፡፡ ሁሌ በካፌ መቀጣጠር ጤነኝነት አይደለም፡፡ የዘመኑ ሴቶች ደግሞ "መላ" የሌለውን ወንድ ስልክ ጥሪም አያነሱም መሰለኝ፡፡ ራስን ሆኖ አለመገኘት ችግር ሴቶችምጋ አለ፡፡ ፍቅርን ሳይሆን ፍትፍትን የሚወዱ ይበዛሉ፡፡ በአሁኑ ዘመን ሴቶች እንጂ ሚስቶች ጥቂት ናቸው፡፡ ከዛ ውስጥ ልባም ሚስት ማግኘት ምን ያህል ከባድ ነው? ቃሉ ልባም ሚስት ማን ያገኛል/ያገባል ይላል፤ መልሱ ልባም ባል ነው፡፡ ጌታ ሆይ ልባም ባሎች ልባም ሚስቶችን እንዲያገቡ እርዳቸው?

3. ራስ ወዳድነት

እውነተኛ ፍቅር ራስ ወዳድ አይደለም፡፡ ለሌሎች የሚኖር፤ ሌሎችን ለመጥቀም የሚያስብ ነው፡፡ በእጮኝነት ህይወት ውስጥ ከባድ ፈተና "ከእሱ/ሷ ምን እጠቀማለው?" የሚለው ጥያቄ እየጎላ

ሲለሚሰማ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ወደ ጊጭት ያመራል፡፡ ራስ ወዳድነትን አስወግደን "ምን ልርዳት?" ወይም "ምን ልርዳው?" በሚል አዕምሮ/Mentality መመላለስ አለብን፡፡

4. **ስደት-** ቤተሰብ በልጃቸው እጮኝነት ካልተደሰቱ የአቋርጡ ጥሪያቸውን በተለያዩ መንገድ ይገልጻለ፡፡ ይህ ደግሞ ለእጮኝነት ህይወት ትልቅ ተግዳሮት ነው፡፡

5. **ማነጅመንት-** ማነጅመንት የገንዘብና የጊዜ አስተዳደር ነው፡፡ እጮኝነት የማነጅመንት ጥበብ ይጠይቃል፡፡

ምዕራፍ 3 ጋብቻ

የጋብቻ ትርጉም

"Marriage is Commitment, Not Experiment." (Derek Prince)

ጋብቻ ተሰርቶ አይጠብቀንም፤ እኛ ነን የምንሰራው፡፡ አባትንና እናትን መተው፤ ከሚስት ጋር መጣበቅ እና አንድ ስጋ መሆን ጋብቻን ሙሉ የሚያደርግ መመዘኛ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚለውን ሀሳቡን አሁንም አልለወጠም፡፡ ስለዚህ አባታችን መልካም አይደለም ያለውን እኛም መልካም አይደለም ማለት አለብን፡፡

በዘፍ 2፡21 ከአዳም ጎን አጥንት ወስዶ ሔዋንን ፈጠራት ይለናል፡፡ ወስዶ የሚለውን ቃል በደንብ አስተውሉ፡፡ ኢሳያስ 66፡1 ላይ እግዚአብሔር ሰማይ ዙፋኑ፤ ምድር የእግሩ መረገጫ ነው ይላል፡፡ በመጀመሪያ ጋብቻ ጊዜ እግዚአብሔር ወደ ምድር በክብር ተገልጦ በሰርጋቸው ታድሞ ነበር፡፡ ከዚህ የምንረዳው ጋብቻ ምን ያህል ክቡር መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ጋብቻ ቤተክርስቲያን ከመቋቋሟም ቀድሞ የጀመረ በምድር የመጀመሪያው ተቋም ነው፡፡

ጋብቻ ማለት፡-

1. ቃልኪዳናዊ የሆነ በተቃራኒ ጾታ መካከል የሚደረግ የመንፈስ፣ የነፍስና የስጋ አንድነት ነው፡፡
2. በእግዚአብሔር የተቀደሰ፤ ከእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ በረከትና ቃል ኪዳን ነው፡፡
3. እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ የተቃራኒ ጾታ መጣመር ነው፡፡ በአፅዱ ሦስቱ የተገመዱበት የሦስትዮሽ ዓለም ነው(መክ 4፡12)፡፡
4. ጋብቻ በጋራ ጥረትና አብሮ በመሆን የሚዳብር የዕድሜ ልክ ትምህርት ቤት ነው፡፡

የጋብቻ ዓላማ

የጋብቻ ዓላማ ማለት ጋብቻ የተመሰረተበት ምክንያት ማለት ሲሆን፡፡ ጋብቻ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

1ኛ መለኮታዊ ተቋም ማቋቋም

የጋብቻ የመጀመሪያው ዓላማ መለኮታዊ ተቋም ማቋቋም ነው፡፡ በጋብቻ ጠንካራ መተማመን እንዲኖርና በትዳራችን ስኬታማ ለመሆን ከተፈለገ የሦስትዮሽ ግንኙነት እንዲጠብቅ ግድ ይላል፡፡ ባልና ሚስት በግላቸው ከእግዚአብሔር ጋር ጤናማ ግንኙነት ሲኖራቸው እርስ በእርስ እንደ ባልና ሚስት የሚኖራቸው ግንኙነት ዘላቂና አስተማማኝ ይሆናል፡፡ **"...በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም።" (መክ 4፡12)**

ባል+ሚስት+እግዚአብሔር=ስኬታማ ጋብቻ

ባል ማሰብ ያለበት እንዴት ሚስቴን ልጥቀማት በማለት እንጂ እንዴት ልጠቀማት በማለት አይሁን፡፡ በመጥቀም ውስጥ መጠቀም እንዳለ መዘንጋት የለብንም፡፡ ባልና ሚስት የሚተጋገዙት በመንፈስ በነፍስና በስጋቸው ነው፡፡ ትክክለኛ ጋብቻ መንፈሳዊ ያልሆነን ሰው መንፈሳዊ ያደርጋል እንጂ ዓለማዊ አያደርግም፡፡ ምክንያቱም ጋብቻ መተጋገዝ በመሆኑ፡፡

"አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል። ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና፤ አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት። (መክ 4፡9-10)

የጋብቻ ዓላማ ያልሆኑ ነገሮች

1. ግብረ ስጋ ግንኙነት የጋብቻ ዓላማ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ያጋባው እንዲደሰቱ ብሎ አይደለም፤ ከተጋቡ ላይቀር ይደሰታሉ እንጂ፡፡ በሌላ አገላለጽ ምግብ የምንበላው ለመደሰት ብለን አይደለም፡፡ ከበላን ላይቀር እንደሰታለን፡፡ ስለዚህ የጋብቻ ዓላማ መደሰት አይደለም፡፡ ለምሳሌ አዳም ሔዋን ከመፈጠሯም በፊት በመንፈስ ቅዱስ ይደሰት ነበር፡፡

2. ከዝሙት ጠንቅ ማምለጥ የጋብቻ ዓላማ ሳይሆን የጋብቻ በረከት ነው፡፡ ሰዎች ጋብቻን መመስረት ያለባቸው ከዝሙት ጠንቅ ለማምለጥ በሚለው ሀሳብ መሆን የለበትም፡፡ ዝሙት ውድቀት ያመጣው ውጤት ነው፡፡ አዳም ሔዋንን ያገባት ከዝሙት ለማምለጥ አይደለም፡፡

የባልና የሚስት ኃላፊነቶች

ባሎች የራሳቸውን ድርሻ ካልተወጡ፤ ሚስቶችም ደግሞ የራሳቸውን ድርሻ ካልተወጡ በመካከላቸው ግጭት ይፈጠራል፡፡ የቤተሰብ መጋጨት ተያይዞ ወደ ቤተክርስቲያን ይደርሳል፡፡ ስለዚህ መፍትሄው እያንዳንዳችን ኃላፊነታችንን ማወቅና ማድረግ ነው፡፡

<u>የባል ኃላፊነቶች</u>

1. **መንፈሳዊ መሪ-** የባል መንፈሳዊ መሪ ክርስቶስ ነው፡፡ የሚስት መንፈሳዊ መሪ ደግሞ ባል ነው፤ በሌላ አገላለጽ ክርስቶስ ሚስትን የሚያየው በባል በኩል ነው፡፡ ለሚስትና ለባል የተለያየ መንፈሳዊ አባት ሊኖራቸው አይገባልም፡፡ የሚስት መንፈሳዊ መሪ/አባት ባል ነው፤ የባል መንፈሳዊ መሪ ሌላ ሊሆን ይችላል፡፡

2. **የመጨረሻ ውሳኔ መወሰን-** በምንም ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጠው ባል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለባል አንድ ኃላፊነት ይጨምራል፡፡ እርሱም በምንም ጉዳይ ሚስትን ማማከርና ሀሳቧን መስማት አለበት፡፡

3. **ሚስቱን መንከባከብ**

4. **ሚስቱን ማድነቅ- "...ሥራዎችዋም በሸንጎ ያመስግኑአት።" (ምሳ 31፡31)**

5. **ሚስቱን ማፍቀር-** የሚስት የመጀመሪያ ፍላጎት ወሲብ ሳይሆን ፍቅር ነው፡፡ የባል ደግሞ የዚሁ ተቃራኒ ነው፡፡ ሚስት በጆሮ የሚነገራትና በተግባር የሚገለጥ ፍቅር ካላየች ሌላው ሁሉ የተሟላ እንኳ ቢሆንም ግራ መጋባቷ አይቀርም፡፡

   ባሎች ሆይ! የሚስቶቻችሁን እግር ታጥባላችሁ? በባህላዊ አመለካከት ይህን ማድረግ ሞኝነትና ውርደት ቢመስልም እንኳን የሚስትን እግር ማጠብ በእግዚአብሔር ፍት ጥበብ ነው፡፡

<u>የሚስት ኃላፊነቶች</u>

1. **ለባሏ መገዛት-** ሚስት ለባል የሚትገዛው ስለምወዳት ነው፡፡ ባል ቀድሞ በደንብ ካልወደዳት ለሚስት መገዛት ይከብዳታል፡፡ እርሷም ደግሞ ከፍቅር የተነሳ ለባሏ መገዛት አለባት፡፡ ቤተክርስቲያን በግድ ሳይሆን በክርስቶስ ፍቅር ተማርካ በውዴታ እንደምገዛለት ሁሉ ሚስትም ለባሏ በፍቅር ተሸንፋ ሊትገዛለት ይገባል፡፡

   እግዚአብሔር ሔዋንን ለመፍጠር ከአዳም ጎን አጥንት ወስዶ ነበር፡፡ ከእግሩ አጥንት አልወሰደም፡፡ ስለዚህ ሚስት ከጎን ያለች ናት እንጂ ከእግር በታች ያለች አይደለችም፡፡ ሚስት ረዳት ናት ሲባል የበታች ናት ማለት አይደለም፡፡ ይልቁን ረዳት የሚያስፈልገው ሙሉ ላልሆነ ሰው ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የመጣው አማኞችን ለመርዳት/ለማጽናናት ነው፡፡ ስለዚህ ሚስት ረዳት ናት ስንል ታንሳለች ማለት አይደለም፡፡

   > ለባሏ የማትገዛው ሚስት ያለችበት ቤተሰብ ካፕቴን ሳይኖረው በማዕበል መሐል እንዳለ መርከብ ነው፡፡ ጋኑን ለመግፊት ቁልፍ ለጋኑ መገዛት አለበት፡፡ ልክ እንደዚሁ በትዳር ህይወት ለሚፈጠሩ ለማንኛውም ችግሮች የሚስት መገዛት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ እንዲያውም አለመገዛት እርግማን ነው(ዘፍ 3፡16)፡፡

2. **ስለ ባሏ መማለድ-** ባልና ሚስት ድንቅ የጋብቻ አማካሪ ቢኖራቸውም፤ ብዙ የትዳር ኮርሶችን ቢማሩም፤ ብዙ መጽሐፍ ቢያነቡም በትዳራቸው እግዚአብሔርን መፍራት ከሌለ ባዶ ነው፡፡ ስለ ባሏ የምትማልድ ሚስት ልባም ሚስት ናት፡፡

3. **ባሏን ማገዝ-** የባሏን ራዕይ መደገፍና ከጎን መቆም አለባት፡፡ ለራሷ ራዕይ ቢኖራት እንኳ በግልጽ በመናገር አብረው መስራት አለባቸው፡፡

ተግባቦት በትዳር ውስጥ

በባለትዳሮች መካከል ያለው ግንኙነት ሦስት አቅጣጫዎች አሉት፡፡ እነዚህን ግንኙነቶችን ማጠናከር ከሁለቱም ይጠበቃል፡፡

1. የባልና የሚስትነት ግንኙነት (ዘፍ 2፡24)
2. የወንድምና የእህትነት ግንኙነት (1ኛ ቆሮ 9፡5)
3. ጓደኝነት (ሚል 2፡14-16)

በባልና በሚስት መካከል ተግባቦት ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው

- በመነጋገር፣
- በመደማመጥና፣
- በመረዳዳት ነው።።

<u>የተግባቦት ተግዳሮቶች፡-</u>

1. **ፍርሃት-** ባል ሚስትን በምንም ጉዳይ መፍራት የለበትም።። ሚስትም እንዲሁ መፍራት የለባትም።። ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል(1ኛ ዮሐ 4፡18)።።
2. **አለመደማመጥ-** አለመደማመጥ የጋብቻ አሲድ ተብሎ ይጠራል።።
3. **ባተለነት-** በቂ ጊዜ ለትዳር ጓደኛ አለመስጠት (ለመዝናናት፣ ለወሲብ ግንኙነት፣ ፍቅርን በቃላት ለመግለጽ፣ ለመጸለይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት)።።
4. **ለቅሶ፣ ቁጣና ኩርፊያ-** ሦስቱ የትዳር ቦምቦች በመባይ ይታወቃሉ።።
5. **ይቅርታ አለማድረግ**
6. **በሰዎች ፊት መቀዋወምና መናናቅ**
7. **አብሮ አለመጸለይና ቃሉን በጋራ አለማጥናት**

የጋብቻ ህይወት እውነታዎች

እውነት 1 መልኩና መጠኑ ይለያያል እንጂ በሁሉም ትዳር ግጭት አለ።።

እውነት 2 በትዳራቸው እስከ መጨረሻው የሚዘልቁና የማይዘልቁ ልዩነታቸው ቅራኔን በአግባቡ የመፍታትና ያለመፍታት ጉዳይ ብቻ ነው።።

እውነት 3 የአገልግሎት ስኬት የትዳር ህይወት ስኬት ውጤት ነው።።

እውነት 4 አባት በልጆቹ ለመወደድ ከፈለገ ሚስቱን ማፍቀር አለበት።። በልጆቹም ፊት ስለእናታቸው መልካምነት መናገር አለበት።።

የጋብቻ ህይወት መርሆዎች

1. **ይቅርታ-** ጥሩ የትዳር ጓደኛ የሚሰራ እንጂ የሚፈጠር አለመሆኑን ማወቅ ለትዳር ህይወት ቁልፍ ነው።። የሚሰራው ደግሞ በይቅርታና በይቅርታ ብቻ ነው።።
2. **አጋፔ ፍቅር**
3. **መቻቻል**

4. ግልጽነት
5. መከባበርና መደማመጥ
6. ህብረት

የጋብቻ ህይወት በረከቶች

1. **የፍቅር ህይወት-** የፍቅር ቃላት መለዋወጥ ለጋብቻ ህይወት ወሳኝ ነው። ከፍቅር ቃላት መካከል ለሚስት ቢሆን "እወድሻለው፣ አፈቅርሻለው፣ አከብርሻለው፣ ማሬ፣ ፍቅሬ.....።"

2. **መተጋገዝ-** በጋብቻ ውስጥ እውነተኛ የሆነ ፍቅርና መደጋገፍ አለ። መተጋገዝ እርስ በርስ አቅምን ለማጎልበትና ለመንፈሳዊ ህይወት ዕድገት በጣም አስፈላጊ ነው። ህዘናችንን ለሌላው ስናካፍለው በግማሽ ይቀንሳል፣ ደስታችንን ስናካፍል ደግሞ በእጥፍ ይጨምራል ይላሉ ነጮች። ባልና ሚስት አንዱ የሌላውን ተፈጥሮአዊ፣ መንፈሳዊና ሙያዊ አቅም ለማሳደግና ለመጠቀም እንዲችሉ የጋብቻ ጥምረት ይረዳቸዋል። በጋብቻ ህይወት ውስጥ አንዱ ሌላውን ያበረታታል፣ ይደግፋል፣ እርስ በእርስ ይጸልያሉ፣ ይተናነጻሉ፣ ይመካከራሉ፣ የምስጋናና የአድናቆት ቃል ይለዋወጣሉ።

3. **አምልኮ-** እግዚአብሔር የሚመለከው በመንፈስና በእውነት ነው።ጋብቻ በእውነት እግዚአብሔርን የምናመልክበት መንገድ ነው(ዕብ 13፡4)። ስለዚህ ጋብቻ አምልኮ ነው።

4. **ወሲባዊ ፍላጎትን በጤናማ ሁኔታ ማሟላት-** ጌታ እግዚአብሔር ወንዶችንና ሴቶችን ከነመራቢያ አካላቸውና ከጾታ ፍላጎታቸው ጋር ፈጠረ። በመሆኑም የወንድነት የባህሪ ሰጪ ሆርሞን/ቴስቴስትሮን እና የሴትነት ባህሪ ሰጪ ሆርሞን/ፕሮጀስትሮን የተባለ ንጥረ ነገሮችን በተፈጥሮ በሁለቱም ጾታዎች ውስጥ ያስቀመጠው እግዚአብሔር ነው። የተቃራኒ ጾታ መፈላለግ እግዚአብሔር ከውድቀት በፊት በሰዎች ያስቀመጠው በመሆኑ በአግባቡ መምራት ያስፈልጋል። ወሲብ በራሱ ቅዱስም እርኩስም አይደለም።

5. **መዋለድ**

የጋብቻ ህይወት ተግዳሮቶች

የጋብቻ ህይወት ተግዳሮቶች ሁሉም ወደ ፍቺ የሚያደርሱ በመሆናቸው ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ፍቺ እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው።

1. **ሁለት ራዕይ በአንድ ቤት-** ባልና ሚስት ሁለት ራዕይ ቢኖራቸው ተስማምተው በአንድነት ራዕያቸውን አጠቃልለው በህብረት ማስቀጠል አለባቸው። በትንሹ የሚስት ራዕይ የባሏን ራዕይ ፊጻሜ ማየት ነው። ከባሏ ሌላ ራዕይ ቢኖራት በግልጽ በመናገርና አብራ ለመስራት መወሰን አለባት። ያለበለዚያ መለያየት ይሆናል። Di/ሁለት ሲሆን ራዕይ ደግሞ Vision ነው። ሁለቱን የእንግሊዘኛ ቃላትን ስናገኛኝ፣ ሁለት ራዕይ በአንድ ቤት ውስጥ Division/መለያየት ይፈጥራል። Division ደግሞ ወደ Divorse/ፍቺ ያመራል። ለዚህ ችግር መፍትሄው መስማማትና መደመር ነው።

2. **አብሮ ያለመኖር ችግር**- በስራ ወይም በትምህርት ምክንያት በተለያየ ሀገር መኖር ለክርስቲያን ባልና ሚስቶች በፊጹም መልካም አይደለም፡፡ ምክንያቱም በሁለቱ መካከል አለመተማመን ጠላት ሊዘራ ይችላል፡፡ የኃላፊነት ጫና በአንዱ ላይ ይደራረባል፡፡ የዝሙት ኃጢአት ፈተና ይበዛል፡፡ በአንጻሩ ግን ባልና ሚስት አብረው በመኖራቸው ብዙ መልካም ነገር ሰለሚያተርፉ ቤተክርስቲያን ተለያይቶ መኖርን አትደግፍም፡፡

3. **የልጆች አስተዳደግ**- ልጆችን እንደባህሪያቸው መቅጣት አስፈላጊ ነው፡፡ ልጆችን ማበላለጥ አይገባም፡፡ ቅጣትም ቢሆን በመስማማት መቅጣት አለባቸው እንጂ አንዱ ሲቀጣ ሌላው ጣልቃ የሚገባ ከሆነ የቤተሰቡን አንድነት ያናጋል፡፡ ልጆች ለእግዚአብሔር ክብር እንዲኖሩ ማስተማር የወላጆች ኃላፊነት ነው፡፡

4. **የዘመድ አያያዝ ችግር**- የእግዚአብሔር ቃል ቤተሰቦቻችንና ዘመዶቻችንን እንድናከብራቸውና እንድንወዳቸው ይነግረናል፡፡ በዘመድ ጣልቃ መግባት ምክንያት ትዳራቸው የፈረሰባቸው ብዙ ናቸው፡፡ ዘመዶቻችን ባለቤቶቻችንን(ባል ወይም ሚስት) ሲያጥላሉ መገሰጽ አለብን እንጂ ፊት መስጠትና ከእነርሱ ጋር ተስማምተን ስም ማጥፋት ፈጽሞ ተገቢ አይደለም፡፡ ደግሞም መልካም ነገር በዘመዶቻችን ፊት መግለጽ አለብን፡፡ የትዳር ጓደኛችንን ሳናማክርና ሳንስማማ ለዘመዶቻችን ስጦታ መስጠትም ሆነ ማስጠጋት ትዳርን ቀስ በቀስ ሊያናጋ ስለሚችል ሁሉን በመስማማት ማድረግ መልካም ነው፡፡ እንዲያውም ዘመድ አብሮ ባይኖር ይመረጣል፡፡ ለማገዝ ከተፈለገም ባለበት ሆኖ በመስማማት ማገዝ አስፈላጊ ነው፡፡

5. **የወሲብ ግንኙነት ችግር**- ወሲብ የጋብቻ ፍቅር የሚገለጽበት አይነተኛ ስፍራ ነው(ምሳ 5፡18-19)፡፡ የመጀመሪያዎቹ ተጋቢዎች አዳምና ሔዋን ስለፈጸሙት ወሲብ በዘፍጥረት 4፡1 ላይ እናነባለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ሊያስተምረን በማያፍርበት ጉዳይ እኛም ልናፍርበት አይገባም፡፡ በባህል ተጽዕኖ ምክንያት የወሲብ ጉዳይ በቤተክርስቲያን ይቅርና በባልና በሚስት መካከልም በግልጽነት የማይነሳ ጉዳይ ሆኗል፡፡ በተለይ በሀገራችን በኢትዮጵያ፡፡

   ስለ ወሲብ ልቅ የሆኑ፣ ግልጸኛና ድብቅ የሆኑ ሰዎች አሉ፡፡ መንፈሳዊ ሰው ግልጸኛ ነው፡፡ ስለዚህ በወሲብ ጉዳይ ባልና ሚስት በግልጽነት መነጋገር ይኖርባቸዋል፡፡ ምናልባት በይሉኝታ ምክንያት የሚደባበቁት የወሲብ ስሜት ሊኖር አይገባም፡፡ ከሆነ ጋብቻው ወደ አደጋ እየሄደ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በወሲብ ጉዳይ ባልና ሚስት ችግር ከሌለባቸው ሌላ ማንኛውንም ችግር መቋቋም ይችላሉ፡፡ ለዚህ ሁሉ መፍትሄው በግልጽ መነጋገር ነው፡፡ ባል የሚስቱን ስሜት በጥንቃቄ ሊያጠና፣ ሚስትም የባሏን ስሜት ልታውቅና ልመካከሩበት ይገባል፡፡

   በወሲብ ግንኙነት ችግር ሲኖር ከሁለት አንዱ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የሚጠቁም ምልክት ያሳያል፡፡ "አሞኛል፣ በመኝታ ጊዜ ስራ በመስራት፣ ጀርባ ሰጥቶ መተኛት እና የመሳሰሉ የወሲብ ችግር መኖሩን የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው፡፡" ቁጣም ካለ መጨረስና የወሲብ መርካት ደረጃ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

   የወንድ የስሜት ሆርሞን(በደስታም ሆነ፣ በፍርሃት ጊዜ) ለወሲብ የተዘጋጀ ነው፡፡ የሴቶች ግን ይለያል፣ ስሜታቸው በተፈጥሮ ዑደት ስለሚመራ ወቅት አላቸው፡፡ በወር አበባ ሂደት ከ1-14 ቀን ድረስ ስሜታቸው ዝግጁ ሲሆን፣ ከ14-28 ደግሞ ለወሲብ ይዘገያል፡፡ በመሆኑም

ሚስት አንዳንድ ጊዜ ከተፈጥሮ ባህሪይ የተነሳ ለወሲብ ዝግጁና ፈቃደኛም ባትሆን መፍረድ አይገባም፡፡ ይልቅስ መረዳዳት ያስፈልጋል፡፡

6. **አለመታመን**- በዝሙት ኃጢአት ባልና ሚስት አንዱ ሌላውን የሚጠራጠር ከሆነ ሁልጊዜም ሌላ ተቀጣጣይ ችግር ተከትሎ ይመጣል፡፡ ለዚህም መፍትሄው ፍቺ ሳይሆን በይቅርታ መቀበል ነው፡፡

7. **አማካሪ አለማወቅ**- በትዳር ጉዳይ ችግር ሲፈጠር ሚስትም ትሁን ባል፣ የትዳር ትክክለኛ አማካሪ ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር ችግሩን ማቅረብ አለባቸው፡፡ በመቀጠል ባልና ሚስት በጉዳዩ ዙሪያ ቢመካከሩ መልካም ነው፡፡ አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ መንፈሳዊ ወደሆነ አማካሪ ለምክር መቅረብ ይሻላል፡፡ በዚህ ሁሉ ግን የትዳር ዓለም የእግዚአብሔር፣ የባልና የሚስት ዓለም በመሆኑ ውሳኔ መወሰን ያለባቸው በመስማማት መሆን አለበት፡፡

8. **ግልጸኛ አለመሆን**- ከተሰወረ ፍቅር የተገለጠ ጥላቻ ይሻላል፡፡ የጋብቻ ህይወት የግልጽነት ህይወት ነው፡፡ የትዳር ጥንካሬ የሚለካው በባልና በሚስት መካከል ባለው ግልጽና ጤናማ ንግግር ነው፡፡ ስለዚህ በእፍኝነት ጊዜ ውስጥ ግልጸኛ የሆኑ ሰዎች በትዳራቸውም ግልጸኛ እንደሚሆኑ መገመት ቀላል ነው፡፡ አዳምና ሔዋን "ራቁታቸውን ነበሩ፣ አይተፋፈሩም ነበር"(ዘፍ 2፡25) ይህ ማለት የአካል ራቁትነት ብቻ ሳይሆን የውስጥ ግልጽነት ነው፡፡ በተለይ ባሎች ጆሮአቸውን ሰጥተው ሚስቶቻቸውን መስማትና በግልነት መነጋገር አለባቸው፡፡

9. **ፉክክር**- የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል ይላሉ አባቶች፡፡ በትዳር ህይወት ውስጥ ያለ ፉክክር ትዳርን ፍቅር ያቀጭጫል፡፡ አካልን ይሰነጥቃል፡፡ ምክንያቱም ባልና ሚስት በትዳር አንድ አካል ሲለሚሆኑ ነው፡፡ ተስማምተው እስከተጋቡ ድረስ እኔ እበልጣለው፣ ምን ያንሳል እንተያያለን፡፡ ከጠላታችን ዲያቢሎስ ጋር እንድንተያይ ያደርገናል፡፡

10. **ቅናት**

ምዕራፍ 4 የቤተሰብ ህይወት

ጋብቻ ለቤተሰብ መሰረት ነው። ጋብቻ ከሌለ ቤተሰብም የለም። ጋብቻ ሁለት ሰዎችን ሲያካትት ቤተሰብ ደግሞ ብዙ ሰዎችን ያቀፈ ሊሆን ይችላል። የአንዲት ቤተክርስቲያን ህልውናና ጥንካሬው ቤተሰብ ነው። ምክንያቱም ቤተሰብ ትንሿ ቤተክርስቲያን ናት። ቤተሰብ አነስተኛ ማህበራዊ ተቋምም ናት። ቤተክርስቲያን የሦስት አካላት ድምር ናት እነርሱም የመጋቢ፣ የዲያቆንና የምዕመናን ሲሆን በቤተሰብ ደግሞ አባት እንደ መጋቢ፣ እናት እንደ ዲያቆን፣ ልጆችና ሌሎች እንደ ምዕመናን ናቸው። ስለዚህ ቤተሰብን ትንሿ ቤተክርስቲያን ማለት እንችላለን።

የአባትና የእናት ኃላፊነቶች

<u>የአባት ኃላፊነቶች</u>

ወንድ ባልና አባት ይሆናል። ባል በመሆኑ የራሱ ኃላፊነት አለው እንዲሁም ደግሞ አባት በመሆኑ ኃላፊነት አለው። ባልነቱ ለሚስቱ ብቻ ሲሆን አባትነቱ ግን ለቤተሰቡ በሙሉ ነው።

1. **እንደ ንጉስ-** ለቤቱ ህግና ስርዓት ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል። መጽሐፍ ቅዱስ አባቶች ልጆቻቸውን እንዲመሩ ያዛል። መምራት ማሰልጠንን ያጠቃልላል። ለምሳሌ አባት ካጠፋ ልጆችን ይቅርታ በመጠየቅ ይቅርታን እንዲለምዱ ማድረግ ይችላል። ምክንያቱም ልጆች ትናንሽ ህዝቦች ናቸው እንጂ አናሳዎች አይደሉም። **"ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን...።" (1ኛ ጢሞ 5፡8) "ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።" (ምሳ 22፡6)**

2. **እንደ ነብይ-** እግዚአብሔርን ወክሎ በቤተሰብ ዘንድ ይቆማል። ኢያሱ እኔና ቤተ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን ብሎ እግዚአብሔርን ወክሎ ስለ ቤተሰቡ ቆመ(ኢያ 24፡15)።

3. **እንደ ካህን-** ቤተሰቡን ወክሎ በእግዚአብሔር ዘንድ ይቆማል። ኢዮብ ስለ ቤተሰቡ በእግዚአብሔር ዘንድ ዕለት ተዕለት መስዋዕት ያቀርብ ነበረ(ኢዮ 1፡5)።

<u>የእናት ኃላፊነቶች</u>

ሴት ሚስትና እናት ትሆናለች። ሚስት በመሆኗ የራሷ ኃላፊነት አላት እንዲሁም ደግሞ እናት በመሆኗ ኃላፊነት አላት። ሚስትነቷ ለባሏ ብቻ ሲሆን እናትነቷ ግን ለቤተሰቡ በሙሉ ነው።

1. **ቤተሰብን መንከባከብ-** የቤተሰብ ህይወት ሙሉ በሙሉ የምታስተዳድር የምትከታተልና የምትቆጣጠር እናት ናት።

2. **ልጆችን ማሳደግ-** ልጆችን ማሳደግ በዋናነት የእናት ኃላፊነት ነው። ልጆች አባታቸውን እንዲከተሉ ታደርጋለች።

ህጻናትን የማሳደግ ጥበብ

1. **ፍቅርን መስጠት-** *በመሳም፣ በማቀፍ፣ በማጉረስ፣ በመሸከምና አስፈላጊ ነገሮችን በመግዛት*
2. **ጠንካራ ጎናቸውን በመንገር**
3. **ደካማ ጎናቸውን ደጋግማችሁ አትተቹ**
4. **አብሮ በመጸለይና በመባረክ**
5. **ማበረታታት**
6. **በመቆጣት**
7. **መውደድና መቆጣጠር**
8. **ትልቅነትን ማወጅ**

ለልጆች አታድርጉ!

1ኛ ሌላ ሰው እንዲቀጣ

2ኛ እንዲማረሩ አትፍቀዱ

3ኛ አባካኝ አታድርጉ

4ኛ ያለ በቂ ምክንያት ገንዘብ አትስጡ

5ኛ በሰው ፊት አትተቹ

6ኛ እንዲሰርቁ አትፍቀዱ

ዋቢ መጽሐፍት

1. Husband And Fathers- Derek Prince
2. Preparing For Marriage- John Piper
3. Model Marriage- Dag Hiward Mills
4. When Wives Walk In Grace- Steve Mcvey
5. God's Blue Print For Happy Home- Lester Sumrall
6. **የእግዚአብሔር ፈቃድ ያለበት ቤተሰብ ኑሮ ዘዴ- አሰፋ ጃቴ**



ልዑልሰገድ ለማ